# ው ይ ይ ት

## ከግንቦት 7 የፍትህ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ

## ክፍል ሁለት

### (ምዕራፍ ሁለት)

### ከኤርትራ መንግስትና ህዝብ ጋር የሚደረግ ግኑኝነትና ትብብር ለምን? (ካለፈው የቀጠለ)

(በ-ኣብርሃም ያየህ)

**ጥቅምት 8 ቀን 2006 ዓ.ም. (October 18, 2013)**

### ኣጭር መ ን ደ ር ደ ር ያ

ባለፈው ሳምንት በለቀቅነው የ"ክፍል-ሁለት" ምዕራፍ-ኣንድ መጣጥፋችን ላይ ኣንባቢዎቻችንን የተሰናበትነው የዚያው ክፍል ኣካል በሆነው በዚሁ "ምዕራፍ ሁለት" ላይ ሁለት ነጥቦች ኣንስተን በመንተነትን ይፋ የምናደርግ መሆናችን ቃል በመግባት እነደነበረ የሚታወስ ነው። ለማስታወስ ያህል፥ ሁለቱ ነጥቦች እንደገና እንጥቀሳቸው።

1. የኤርትራ መንግስት የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ በፌደራሲዮን እንዲተሳሰሩ ፍላጎት ያለው መሆኑን የሚያስረዱልን ተጨማሪ ጭብጦች የምናቀርብ መሆኑን።
2. የኤርትራ መንግስት ያንን መልካም የፌደረሽን ሃሳብ ኣቅርቦ እያለ መለስ ዜናዊ ሃሳቡን ውድቅ ያደረገበት ምክንያት በህወሓትና በራሱ በመለስ ታሪክ ተመርኩዞን ዝርዝር ትንተና የምንሰጥ መሆኑን።

ስለዚህ ሁለቱም ነጥቦች ኣጠር ኣድርገን በቅደም ተከተል እንመለከታቸዋለን።

### የኤርትራ መንግስት የፌደራሲዮን ሃስብ ስለማቅረቡ የሚያስረዱ ተጨማሪ ጭብጦች

ይህኛው ነጥብ ሌላ ማስረጃ ሳያስፈልገው በምዕራፍ ኣንድ ያስቀመጥነውና ኣቶ ኢሳያስ ኣፈወርቂ ከኣሜሪካ ድምፅ ሬድዮ ጋር ያደረገው ቃለመጠይቅ[1] በራሱ በቂ ማስረጃ ነው። ሆኖም፥ ለበለጠ ግንዛቤ ሌሎች ተጨማሪ ጭብጦች ማቅረብ ጠቃሚ ይመስለናል።

እንደ ኣጋጣሚ ሆኖ፥ እኛ ከኤርትራ መንግስት ጋር ተነጋግረን ስራዎቻችን በማስቀጠል ላይ በነበርንበት ጊዜ የኤርትራው ገዢ ፓርቲ (ህግደፍ) ምክር ቤት (የኤርትራ ፓርላማ/ሸንጎ) 14ኛ መደበኛ ጉባኤውን ኣካሂዷል። ከያዝነው ኣርእስት ጋር በተያያዘ ሸንጎው በጉባኤው ማጠቃለያ ላይ ባሳለፈው የውሳኔ መግለጫ ላይ በተራ ቁጥር 6 የሰፈረውን እንመልከት። (እንጠቅሳለን)

---

[1] http://www.awrambatimes.com/wp-content/uploads/Dialogue_with_Ginbot-7_P2_sec_1.pdf (ፕሬዚዳንት ኢሳያስ ከኣሜሪካ ድምፅ ያደረገው ቃለመጠይቅ፤ ገፅ 8።)

> "ከኤርትራ ነፃነት ጋር በ1991 ዓ.ም. በኢትዮጵያ የመጣው ለውጥ በአፍሪካ ቀንድ የጦርነትና የውድመት ዘመን ኣብቅቶ፥ ህዝቦቹ ሰላም በማጣጣም በክልላዊ ውህደት በዓለም ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የነበረንና የሰራንበት ራእይ በአሮጌው ኣስተሳሰብና በጥቂቶች ያልተረጋጋና በራስ ያለመተማመን ባጠቃቸው ወገኖች ለጊዜው ይደናቀፍ እንጂ፥ ይህንን ተከቶ ዘላቂ ሰላምና ብልፅግና ሊያስገኝ የሚችል መንገድ ስለሌለ፥ በኣንድ እጃችን ሳናጨበጭብ የበኩላችን ኣስተዋፅኦ ለማድረግ የሚያውከን ነገር ባለመኖሩ ኣርቀን በመመልከት ለኣካባቢያችን መተጋገዝ በሁነኛ መንገድ ያልተቆጠበ ጥረት እናደርጋለን።" የጥቅሱ መጨረሻ (ኣፅንኦት/ሰረዝ የኛ።)

መልእክቱ ግልፅና ግልፅ ነው። ከላይ በተመለከተው የኤርትራ ሸንጎ  ጉባኤ የውሳኔ መግለጫ ላይ እንደሰፈረው "ህዝቦቹ ሰላም በማጣጣም በክልላዊ ውህደት በዓለም ላይ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የነበረንና የሰራንበት ራእይ በአሮጌው ኣስተሳሰብና በጥቂቶች ያልተረጋጋና በራስ ያለመተማመን ባጠቃቸው ወገኖች ይደናቀፍ እንጂ" የሚለው ኣባባል የኤርትራ መንግስት ቀደም ሲል ለወያነ ስርዓት ኣዲስ ሃሳብ ኣቅርቤ ወያነ በራሱ ምክንያት ኣደናቀፈው ያለበትን ሆኔታ በትክክል ያጠናክረዋል። ከዚህ በተጨማሪ፥ በዚሁ የኤርትራ ሸንጎ የጉባኤ ውሳኔ መግለጫ ላይ "ይህንን ተክቶ [ክልላዊ ውህደትን ተክቶ] ዘላቂ ሰላምና ብልፅግና ሊያስገኝ የሚችል መንገድ ስለሌለ በኣንድ እጃችን ሳናጨበጭብ የበኩላችን ኣስተዋፅኦ ለማድረግ የሚያውከን ነገር ባለመኖሩ ኣርቀን በመመልከት ለኣካባቢያችን መተጋገዝ በሁነኛ መንገድ ያልተቆጠበ ጥረት እናደርጋለን" በሚል በማያወላውል ሆኔታ የሰፈረው ቃል፥ የዚህ መጣጥፍ ኣካል በሆነው በምዕራፍ ኣንድ[2] ላይ የኤርትራው መንግስት ከፍተኛ ልኡክ በዋሺንግተን ስብሰባችን ላይ ከገለፀው የራሱ መንግስት ኣቋም ጋር በትክክል ይስማማል።

በሌላ በኩል ደግሞ፥ የኤርትራው መንግስት ልኡክ ለኛ ከገለፀልን ጋር በሚስማማ መንገድ የኤርትራውን መንግስት ኣምርረው ከሚቃወሙት ወገኖች መካከል ኣንዱ የሆኑትና በኢትዮጵያና በኤርትራ ጉዳይ በስፋት የሚፅፉት እውቁ ምሁር ዶ/ር. ተስፋፅዮን መድሓንየ የሚሉትን እንመልከት። (እንጠቅሳለን)

> "ኣቶ ኢሳያስ ኣፈወርቂና ሌሎች የህዝባዊ ግንባር ለፍትህና ለዲሞክራሲ መሪዎች በሁለቱ ኣገሮች [ኢትዮጵያና ኤርትራ] መካከል ያለው ወሰን ትርጉም የሌለው በመሆን ላይ ነው እስከማለት ደርሰው ነበር። ጥቂት የግንባሩ ከፍተኛ ካድሬዎች በመጨረሻ ኤርትራና ኢትዮጵያ በፌደረሽን መሰረት ላይ የሚተባበሩበት [የሚተሳሰሩበት] ሆኔታ እስከሚፈጠር ድረስ የውህደትና የኮንፌደረሽን መዋቅሮች እየተጠናከሩ መራመድ እንደሚኖራቸው ሃሳብ ሰጥተዋል"[3]
> (የጥቅሱ መጨረሻ። ኣፅንኦት የኛ)

(ዶ/ር ተስፋፅዮን "የህዝባዊ ግንባር ለፍትህና ለዲሞክራሲ" ሲሉ የጠቀሱት ኣሁን በስልጣን ላይ ያለው የኤርትራ ገዢ ፓርቲን (ህግደፍ) ነው። የዶ/ር. ተስፋፅዮን ገለፃ የኤርትራ መንግስት ለወያነ መንግስት ኣቀረብኩት የሚለው የፌደረሽን ሃሳብ ከግጭቱ በፊት ያቀረበ መሆኑን በሚገባ ይገልፀዋል።)

እንግዲህ፥ የዚህ ምዕራፍ የመጀመሪያውን ነጥብ ከማጠቃለላችን በፊት ጭብጦቻችንን ጨምቀን እንያቸው።

---

[2] http://www.awrambatimes.com/wp-content/uploads/Dialogue_with_Ginbot-7_P2_sec_1.pdf (ገፅ 10-11 ይመልከቱ)

[3] ዶ/ር. ተስፋፅዮን መድሓንየን በመጥቀስ "ጦቢያ" መፅሄት በግዕዝ ኣቆጣጠር በህዳር ወር 1994 ዓ.ም. ቅፅ 9 ቁጥር 4 እትም ላይ እንዳሰፈረው።

1. በዚህ በያዝነው "ክፍል ሁለት" በምዕራፍ አንድ ላይ አንደተመለከተው[4] ባንድ በኩል ፕሬዚዳንት ኢሳያስ አፈወርቂ ካሜሪካ ሬዲዮ ጋር ያደረገው ታሪካዊ ቃለመጠይቅና፥ የፕሬዚዳንት ኢሳያስ ቀኝ እጅና የፖለቲካ አማካሪ የሆነው አቶ የማነ ገብረአብ በዋሺንግተኑ ስብሰባችን ላይ የሰጠው ሰፊ ማብራሪያ በማያወላወል መንገድ ሁለት ጭብጦች አስጨብጦናል።
2. በዚህ ምዕራፍ ከላይ እንዳስቀመጥነው፥ የኤርትራው ገዢ ፓርቲ በጉባኤው ውሳኔ ተመስርቶ ያስተላለፈው ኦፊሴላዊ መግለጫና፥ ክቡር ወንድማችን ዶ/ር. ተስፋፅዮን መድሓንዩ በጦቢያ መፅሄት ላይ ባሰፈረው ሐቅ መሰረት ደግሞ ሌሎች ሁለት መጋቢ መረጃዎች ጨብጠናል።

ስለዚህ፥ አራቱንም ጭብጦች አንድ ላይ ተጨምቀው የሚሰጡን የተጣራ ጭብጥ የኤርትራ መንግስት ከግጭቱ በፊት የፌደሬሽኑን ሃሳብ ለመለስ መንግስት ለማቅረቡ የማያጠያይቅ መሆኑን ነው። ከዚህ ጭብጥ ተነስተን ካስራ ሁለት ዓመታት በፊት የተገኘውን መልካም አጋጣሚና ተፈትፍቶ የተዘጋጀውን ምግብ አንቀምስም ብለው ያበላሹትን ባንጠላቸም እንቀየማቸዋለን። ቅያሜ ከጥላቻ መንደር ብዙ የሚርቅ ባይሆንም።

<u>የኤርትራ መንግስት ያቀረበውን የፌደረሽን ሃሳብ መለስ ዜናዊ ለምን አልፈለገውም?</u>

በክፍል ሶስት ምዕራፍ አንድ ላይ እንደጠቀስነው[5]፥ የኤርትራው መንግስት ልኡክ በወያነው ህገመንግስት ላይ የሰፈረውን አንቀፅ 39 አስመልክቶ የገለፀው ቅድመ ሆኔታ ልዩ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ይህ ማለት፥ የህወሓት መሪዎች አሁን በስራ ላይ ያለው የራሳቸው ህገመንግስት መታረም እንደማይፈልጉና ኤርትራና ኢትዮጵያም ማንኛውም ዓይነት ትስስር እንዲኖራቸው ፈፅመው የማይሹ መሆናቸውን በትክክል ያመለክታል ማለት ነው።

ከመዘዘኛው አንቀፅ 39 ጋር በተያያዘ፥ የኤርትራ መንግስት በወያነው ህገመንግስት ላይ እርማት እንዲደረግ የጠየቀበት ምክንያት በቅጡ መረዳት ያስፈልጋል። ኤርትራ በፌደራሲዮን ከኢትዮጵያ ጋር የምትተሳሰር ከሆነ የወያነ ህገመንግስት በኤርትራም ጭምር ተፈፃሚነት ይኖረዋል ማለት ነው። የኤርትራን ጂኦፖለቲካዊና ሌሎች የውስጥ ችግሮች ለሚያውቅ ሰው፥ የወያነ ህገመንግስት በኤርትራ ምድር ተግባራዊ ሲሆን ኤርትራ የምትባል አገር ባጭር ጊዜ ውስጥ እንደምትተራመስ ለመረዳት አያዳግተውም። ስለሆነም፥ የወያነ ህገመንግስት ከኢትዮጵያ ይልቅ ለኤርትራ በእጅጉ አስጊ ይሆናል ማለት ነው። ስለዚህ የኤርትራ መንግስት በወያነ ህገመንግስት ላይ እርማት እንዲደረግ ያቀረበው ቅድመ-ሆኔታ ለኤርትራ ቁልፍ ጥያቄ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ የኤርትራ መንግስት ያደረገው ትልቅ ስህተት ለመለስ መንግስት ያቀረበው የሬፈረንደም ሃሳብና የወያነ ስርዓት አልቀበልም ማለቱን በወቅቱ ለኢትዮጵያ ህዝብ ይፋ ያለማድረጉ ነው። ይህ ቢሆን ኖሮ ለብዙ ህይወት አልቂት ሰበብ የሆነው የባድመ ትርምስ ያለ ምንም ችግር ማስወገድ ይቻል እንደነበር በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። ይሁን እንጂ፥ የኤርትራው ልኡክ ዋሺንግተን ላይ ለኛ እንዳብራራው በዚች አንድ ጉዳይ ምክንያት ብቻ በሁለቱም ስርዓቶች መካከል የነበረውን ሰፊ ግኑኝነት እንዳይበላሽበት ማስፈለጉ እንረዳለን።

በዚህ ሂሳብ የቀረቡልን ምርጫዎች ሁለት ናቸው። አንዱ፥ ህገመንግስቱን በማስተካከል የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ በፌደራሲዮን አስተርሳስሮ ሁለቱም ህዝቦቹ ዘላቂ ሰላምና ብልፅግና እንዲጎናፀፉ ማድረግ ነው። ሁለተኛው ምርጫ ደግሞ፥ አሁን በስራ ላይ ያለው የወያነ ህገመንግስት ሳይነካ ኤርትራም ከኢትዮጵያ ጋር ሳትነካካ ትቀጥል የሚል ነው።

---

[4] http://www.awrambatimes.com/wp-content/uploads/Dialogue_with_Ginbot-7_P2_sec_1.pdf
[5] Ibid: (ገፅ 10-11 ይመልከቱ፤)

የወያነ ስርዓት የመረጠው ሁለተኛውን ነው። ለምን? ቢባል፥ መልሱ ቀላል ነው። የህገመንግስቱ አንቀፅ 39 የወያነ መሪዎች በኢትዮጵያ ምድር አሁን የተቆጣጠሩትን ስልጣን ፈተና ሲገጥመው ትግራይን ከኢትዮጵያ ለማስገንጠል ካላቸው ቋሚ ዓላማ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ነው። ከትግራይ በቀር ለተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ የራሱን ዕድል በራሱ እንዲወስን ማድረግ ያልቻለ ህገመንግስት ከሚታረም ይልቅ፥ በጋራ ብዙ ነገር ሊጠቀም የሚችለው የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ተለያይቶ ይኑር ብሎ የሚመርጥ ስርዓት ደግሞ ድብቅ ዓላማ ያለው በታኝ ስርዓት ነው ብሎ ከመጥራት በቀር ሌላ ስያሜ ሊሰጠው አይቻልም። ስለሆነም፥ ያለ ምንም ጥርጣሬ የመለስና በሱ ጀርባ የተኮለኮሉት የኤርትራ ዝርያ ያላቸው የህወሓት መሪዎች ድብቅ ዓላማ የኢትዮጵያ ህዝብ እርስ በርሱ ተባልቶ የሚበታተንበት ሆኔታ አመቻችቶ ትግራይንም በመገንጠል[6] ኬሌላዋ አገራቸው ከኤርትራ ጋር እንድትቀላቀል ማድረግ መሆኑን መጠራጠር አያስፈልግም።

በአንፃሩ ደግሞ፥ አሁን በስልጣን ላይ ያለው የኤርትራ መንግስት ኤርትራ ከመላዋ ኢትዮጵያ እንጂ ከትግራይ ብቻ እንድትተሳሰር የማይፈልግ ሆኖ መገኘቱ እጅግ የሚያስገርም ክስተት ነው። አሳዛኙ ነገር ደግሞ፥ በትክክለኛ ጊዜ መስራት የማይሆንላቸው የኢትዮጵያ ሊሂቃን (በተለይ የአማራ ሊሂቃን) በፈጠሩብን ሳንካ ምክንያት፥ ባሁኑ ወቅት የወያነ መሪዎች ይህንኑ የኤርትራ መንግስት አቋም ለማክሸፍ ሲሉ በኤርትራ የነሱን ዓላማ ለማስፈፀም የሚመቻቸውን ስርዓት ለማቆም በማቀድ አለ የተባለ የኢትዮጵያ የየብስና የአየር መከላከያ ኃይል በትግራይ ምድር አከማችተው በመጠባበቅ ላይ መሆናቸው ነው።

ያለፈው እልቂት እጅግ የሚፀፅት ቢሆንም፥ አሁንም ሌላ አላስፈላጊ እልቂት ሊያስከትሉ የሚችሉ ችግሮች ተገቢ ትኩረት ሳይሰጥባቸው ፉከራውና ጫጫታው እየቀጠለ መሆኑን ማየታችን በበለጠ ያስቅቃል። ጤነኛ አዕምሮ ያላቸው ኢትዮጵያዊያንና ኤርትራዊያን ዜጎች ካሉ በረጋ መንፈስ፥ በቅንነትና በጥበብ እየሰሩ የጋራ ችግሮቻችንን በጋራ የምንፈታበት መንገድ አሁንም ዝግ ያለመሆኑን መረዳት አለባቸው። የኢትዮጵያና የኤርትራ ህዝብ ችግር የሚፈታው በኛ በኢትዮጵያና በኤርትራ ህዝብ ልጆች ብቻና ብቻ እንደሆነም በትክክል ሊሰመርበት ይገባል። በተረፈ፥ አሁን ለተደቀኑብን ፈተናዎች የዳረጉን ፈረንጆችና ዓረቦች መሆናቸው እየታወቀ ሳለ፥ ለኛ ሰላምና መግባባት ያስገኙልን ይመስል ወደ አልጀርስ፥ ዋሺንግተንና ሄግ ሄደን መማጠን ምንም የምናገኘው ፋይዳ የለም።

ይህ በዚህ እንዳለ፥ ካነሳነው ርእስ ጋር በተያያዘ፥ ሻዕቢያ ከትግሉ ዘመን ጀምሮ ከህወሓት መሪዎች ጋር የነበረውን ሙግት አስመልክተን ጥቂት አንበል።

በተለያዩ ጊዜያቶችና መድረኮች በመጣጥፎቻችንም ጭምር ደግመን ደጋግመን ብንናገረውና ብንፅፈውም ቅሉ፥ በነቃው ህዝብና በተለይም "ሁሉንም ነገር የምናውቀው እኛው ብቻ ነን" ባዮቹ የአማራ ብሄር ሊሂቆቻችን ጎራ ያለው የግምገማ እጥረትና ችግር፥ የህወሓት አመራር ከኤርትራ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ያለው ድብቅ ዓላማ ትግራይ ጭምር ከኢትዮጵያ ለማስገንጠል ካለው የረጅም ጊዜ እቅድ ጋር የተያያዘ መሆኑን ያለመረዳት ነው። በጣም የሚገርመው ደግሞ፥ ሻዕቢያ በተቃራኒው ይህንን የህወሓት መሪዎች እኩይ ዓላማ ሲኮንን የኖረ መሆኑን ስንመለከት ነው። ከኛ ከኢትዮጵያዊያኑ ይበልጥ የትግራይ ሬፑብሊክ የሚባለውን ፈዝ የተቃወመ ሻዕቢያ ነው። ይህንን የሻዕቢያ አመለካከት በተመለከተ መለስ ዜናዊ የሚያወርደውን እርግማን በራሱ በመለስ በተደረሰው "የኤርትራ ትግል ከየት ወዴት" በተሰኘውና ከ300 ገፆች በላይ ያካተተውን መፅሓፍ በማገላበጥ መለስ ሻዕቢያን እንዴት እንደሚያብጠለጥለው መመልከት ይቻላል።

[6] የህወሓት መሪዎች አሁን የተቆጣጠሩትን ስልጣንና የኢትዮጵያ ሃብት የሚያስጥል ፈተና ቢገጥማቸው የህገመንግስታቸው አንቀፅ 39 ተገን በማድረግ ትግራይን ለመገንጠል የሚጠቀሙበት መላምት በተመለከተ፥ የመጣጥፎቻችን የመጨረሻው ክፍል በሆነውና "ምን መደረግ አለበት" በሚለው ርእስ ላይ በዝርዝር ይቀርባል።

መለስ ዜናዊ በዚህ መፅሓፉ ውስጥ በተደጋጋሚ ሻዕቢያን እያብጠለጠለ የሚወርፍበት ምክንያት፥ ሻዕቢያ የትግራይን ከኢትዮጵያ መገንጠል ስለሚቃወም ነው። ለአብነት ያህል መለስ በራሱ መፅሓፍ ላይ የሚናገረውን ቀንጭበን እንመልከት። (እንጠቅሳለን)።

"ህግሓኤ [ሻዕቢያ] የራስን ዕድል በራስ የመወሰን ጥያቄ አስመልክቶ ያቀረበው አስተያየት እንደሚከተለው ሊጠቃለል ይችላል። ...በኢትዮጵያ ባለው ተጨባጭ ሆኔታ ይህ መብት የዲሞክራቲክ አንድነት መብት እንጂ በመገንጠል የገዛ ራስን መንግስት መምስረት የመቻልን መብት መጨመር አይችልም። ምክንያቱም በኢትዮጵያ አንድ ፀረ ህዝብ የሆነ መንግስት እስካለ ድረስ አንዲት ብሄር ታግላ የገዛ ራሷ ነፃ የሆነ መንግስት የማቋቋም አቅምና ችሎታ አይኖራትም። ፀረ ህዝብ የሆነው መንግስት ተደምስሶ ፍትህ የነገሰበት ስርዓት ከተመሰረተ ደግሞ የመገንጠል ጥያቄ አይነሳም፤ ዲሞክራቲክ አንድነት ብቻ ነው መኖር ያለበትና የሚገባው። ስለዚህ ህወሓት እንደ አንድ አማራጭ አድርጎ በፕሮግራሙ ማስፈር የሚገባው የዲሞክራቲክ አንድነት ምርጫን እንጂ ድሞክራሲያዊ አንድነት ወይም መገንጠል የሚሉትን ሁለት አማራጮች ማስቀመጥ የለበትም። እንዲህ ማድረጉ ደግሞ ስህተት ነው የሚል ነበር።"[7]

እንግዲህ አቶ መለስ የሚነግረንና ሲቃወመውም የኖረው ይህንን ከላይ የጠቀስነው ወርቅ የሆነ የሻዕቢያ አቋምን ነው። በጣም የሚገርመው ደግሞ፥ ይህ የሻዕቢያ አቋም የኛም አቋም መሆኑ ነው። እንደዚህ ያለ አቋም ባለን የትግራይ ተወላጆች ላይ፥ የህወሓት መሪዎችና እንደነ ሰሎሞን ዑንቋይ ያሉ ከርሳም ካድሬዎች፥ እኛን "እንደ አማራ ነው የሚያስቡት፤ የሸዋ ትግሮች ናቸው (ሸዋዊያን ተጋሩ)፤ ታላቋ ኢትዮጵያ (ዓባይ ኢትዮጵያ) ባዮች ናቸው፤" ወዘተ. የሚል ታርጋ ሲለጥፉብን ኖረዋል። ተነግሮ የማያልቀውን የወያነ መሪዎች ጉድ ለጊዜው ቆም አርገን፥ ከላይ ለተጠቀሰው የሻዕቢያ አቋም መለስ ዜናዊ በዚያው መፅሓፉ ላይ የሚለውን እንመልከት።

"ህወሓት ይህን አዲስ የህግሓኤ [የሻዕቢያ] አቋም ፍፁም የተሳሳተና የህዝቦችን የራሳቸውን ዕድል በገዛ ራሳቸው የመወሰን መብት የሚፃረር አቋም መሆኑን ሰፋ ባለ ሆኔታ ተንትኖ ለማስረዳት ሞከረ። በህወሓት በኩል የቀረበው አስተያየት ደግሞ እንደሚከተለው ሊጠቃለል ይችላል። የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት ማለት በማንኛውም ወቅትና ቦታ አንድ ህዝብ መስሎ ከታየው ጋር በአንድነት ሊኖርና መስሎ ካልታየው ደግሞ ሊገነጠል ሙሉ መብት አለው። ይህም መብት ፍትህና ዲሞክራሲ ባልሰፈነበት ስርዓትና ወቅት ተግባራዊ መሆን የሚችል፥ ፍትሃዊ ስርዓት በተመሰረተበት ወቅት ደግሞ ተግባራዊ መሆን የማይችል መብት አይደለም።"[8]

የመለስ አባባል በእጅጉ ግልፅ ስለሆነ የኛ ትንተና የሚያስፈልገው አይመስለንም። ሆኖም፥ የትግራይ ሬፐብሊክ የሚለውን የህወሓት መሪዎች የማይናወጥ አቋምና፥ ይህንን የመገንጠል አቋም አስመልክቶ ሻዕቢያ ገና መንግስት ሳይሆን በጫካው ዘመን ጭምር የነበረው ተቃራኒ አቋም አንድ ጠቃሚ ነገር ያስጨብጠናል። ይኸውም፥ ኤርትራ ነፃ አገር ከሆነች በኋላ የኤርትራ መንግስት ለወያነ መንግስት ካቀረበው የፌደረሽን ሓሳብ ጋር የአንቀፅ 39 እንደ ቅድመ ሆኔታ አድርጎ ማቅረቡ አዲስ አቋም ያለመሆኑን በትክክል የሚያስረዳ መሆኑን ነው።

---

[7] መለስ ጫካ ሳለ ባሳተመው መፅሓፍ "የኤርትራ ህዝብ ትግል ከየት ወዴት" ያማርኛው ቅፅ ገፅ 231-232፤ ወይም አብርሃም ያየህ እንደገና ባሳተመው የመለስ መፅሓፍ ገፅ 170።

[8] Ibid

ካለን ጊዜ ኣኳያ ለቅምሻ ያህል ከመለስ መፅሓፍ ወስደን ትንሽ ማስረጃ ጠቀስን እንጂ የሻዕቢያ የማይናወጥ ኣቋም በመቃወም መለስ በመፅሓፉ ላይ በሻዕቢያ ላይ የሚያወርደው እርግማን ዝርዝር እጅግ ሰፊና ኣስገራሚ ነው። ስለሆነም፥ የህወሓት መሪዎች "የትግራይ ሬፐብሊክ" ራእይና ይህንን ሬፐብሊክ እውን ለማድረግ ደግሞ የኤርትራ ነፃ ኣገር ሆና መቀጠል ለህወሓት መሃንዲሶች ያለው ጠቀሜታ በግልፅ ለመረዳት ይችሉ ዘንድ ኢትዮጵያዊያኖች በተለይ ያማራ ኤሊቶች መፅሓፉን ኣፈላልገው ከተቻለም እንደገና ኣሳትመው በማሰራጨት በእርጋታ እንዲመረምሩት ማድረግ ወሳኝ መሆኑን እናስታውሳለን።

ከዚህ በተጨማሪ፥ የመለስና በመለስ ዙሪያ የተኮለኮሉት ሰዎች ማንነትና መሰሪ ዓላማ በተገቢው ለማስጨበጥ ይረዳን ዘንድ ህወሓትን ከመሰረቱት[9] ጥቂት ሰዎች ኣንዱ የሆነውና በተለያዩ ጊዚያቶች የድርጅቱ ሊቀመንበርና የወታደራዊ ጉዳዮች ኮሚቴ ሰብሳቢ የነበረው ዶ/ር ኣረጋዊ በርሀ (በርሄ) በማሌሊት[10] ምስረታ ማግስት ድርጅቱን ለቆ እንደወጣ "ማሌሊት ዘላይ" በሚል ርእስ ባሰራጨው ሰፊ ፅሑፍ የጠቀሰውን ዋቢ ኣድርገን ብንጠቅስ ጠቃሚ ጭብጥ ሊሰጠን ይችላል። (እንጠቅሳለን)

> "...ለትግሉ መነሻ መመሪያ የሆነ ኣጭር ፕሮግራም ገና ከተማ ውስጥ እያለን በ1967 ዓ.ም. መግቢያ ላይ የተዘጋጀ ሰነድ ነበረን።...ይህ ኣጭር ፕሮግራም በትግርኛ ቋንቋ በግልፅና በማያሻማ መንገድ ያሰመረበት፥ የትግራይ ህዝብ መራራ ብሄራዊ ጭቆና እንደደረሰበት በማመልከት፥ ህዝቡ ብሄራዊ ጭቆናን ለማስወገድና መደባዊ ነፃነቱን ለማረጋገጥ፥ ኣማራጩ ስልት ብሄራዊ ሆኖ ይዘቱ ግን መደባዊ መሆኑን ያነጣጣረ፥ ህዝቡ ዕድሉን በራሱ በመወሰን ፖለቲካዊ መብቱ ተከብሮለት በእኩልነታዊ ኣንድነት ለምትፈጠር ኢትዮጵያ ቀዳሚ ዓላማውና ኣቋሙ ያደረገ የድርጅቱ ሰነድ ነበር። ...ቀዳሚው ፕሮግራማችን ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሆኔታ በመነሳት የትግራይ ህዝብ ብሄራዊ መብቱንና መደባዊ ነፃነቱን ለመጎናፀፍ የሚችለው ከሌሎች የኢትዮጵያ ህዝቦች ጋር በእኩልነት ኣንድነትን ፈጥሮ ሰላምና እድገትን እውን ለማድረግ ያቀደ ዴሞክራሲያዊ የትግል መመሪያ ነበር።
>
> "...ሁሉም እንደሚያውቀው ማኒፌስቶ-68[11] የትግራይ ህዝብ ብሄራዊ ትግል ነፃ የትግራይ ሪፐብሊክ ለመመስረት ያለመ ነበር። ይህ ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ የትግራይ መንግስት የመመስረት ዓላማ ከዚያ ከቀዳሚው ፕሮግራም በይዘቱ የተለየ ኣዲስ ኣመለካከት መሆኑ ነው። ...ማኒፌስቶ-68 ያንን ቀዳሚ ፕሮግራም (ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ) እንዲተካ ማን ኣንቀሳቀሰው? በምን ዓይነት መድረክ ውይይት ተደርጎበት ተወሰነ? ኣርቃቂው፥ ፀሓፊው፥ ኣሳታሚውስ ማነው? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት በወቅቱ

---

[9] በተለያዩ ፅሑፎችና ሚድያዎች መለስ ዜናዊና ስብሓት ነጋ ህወሓት ከመሰረቱ ሰዎች መካከል እንደሆኑ የሚገለፀው ነጭ ውሸት ነው። መለስና ስብሓት ህወሓት ከተመሰረተና የመስከ ትግል ከተጀመረ በኋላ ዘግይተው የተቀላቀሉ በትግራይ የኤርትራ የውስጥ ኣርበኞች ናቸው።

[10] "ማርክሲስት ሌኒንስት ሊግ ትግራይ" (ማሌሊት) በመለስና መሰሎቹ መሪነት በደርግ ውድቀት ዋዜማ በድርቅ የተጎዱትን ወገኖቻችን ለመርዳት ከዓለም ዙሪያ በተገኘ በርካታ ገንዘብ ባክኖባት የተመሰረተች ጭራቅ ዓይነት ድርጅት ናት። በማሌሊት ልደት (ከድርቅ ተጎጂዎች በተመነተፈ ገንዘብ) የተደገሰው ድግስ ስፋትና የተዜሙት መዝሙሮች ብዛት በቁጥር ለማስቀመጥ ከባድ ነው። የማሌሊት መመስረት ዋና ዓላማ የህወሓትን ኣመራር በመቆጣጠር ሊኤርትራ መገንጠል እንቅፋት የሚሆኑትን ለማስወገድ ሆኔታዎችን ለማመቻቸት ነበር። ደርግ ወድቆ እነ መለስ ኤርትራን ካስገነጠሉ በኋላ ማሌሊት የምትባለዋ ጭራቅ የመሞቷን መርዶ ሳይነገረን፥ የቀብር ስንርስርዓቷ ሳይከናወን፥ ኣርባዋንና ተዝካርዋን ሳንበላ የውሃ ሽታ ሆና መቅረቷ የተመሰረተችበትን መሰሪ ምክንያት ምን እንደነበረ ግልፅ ያደርገዋል።

[11] ማኒፌስቶ 68 በመባል የሚታወቀው ኣስገራሚ ሰነድ (ጠቅላላው የህወሓት ኣመራርና ኣባል ሳያውቀው) በድብቅ መለስ ዜናዊ፥ ስብሓት ነጋ፥ ኣባይ ፀሓየና፥ ስዩም መስፍን በግላቸው የፃፉትና በሱዳን ምድር ኣሳትመው የበተኑትና ተግራይ ከኢትዮጵያ ተነጥላ "የትግራይ ሪፐብሊክ" እንደሚመሰረት የሚያበስር ሰነዳቸው ነው።

የነበረውን እንደነበረው በትክክል ማስቀመጥ በኢትዮጵያ ኣብዮት መድረክ በየጊዜው በመነሳት ላሉትና መልስ ላላገኙት ጥያቄዎች በመመለስ ትግሉን ለማራመድና ለማፋጠን ጠቃሚ ሊሆን ይችላል። ...የዚያ ስንኩል ማኒፌስቶ-68 ምንጩ በመሪነት ደረጃ ከነበሩት የድርጅቱ ኣባላት ነበር።...ያንን ስንኩል ማኒፌስቶ ያዘጋጀውና ያሳተመው ኣሁን የማሌሊት ወሳኝ ኣካል ሆኖ ያለና ከድሮ ጀምሮ ኮሚኒስት ኃይል ነበርኩ የሚለው የማሌሊት ያመራር ቡድን[12] ነው። ...ድርጅቱ የማያውቀውን ኮሚቴ የፈጠሩት ኣባይ ፀሃየ (ኣስተባባሪ)፥ መለስ ዜናዊ (ፀሓፊ)፥ ስብሓት ነጋ (ኣማካሪ) በመሆን ጠባብ ብሄራዊ ኣመለካከታቸውና ግላዊ ምኞታቸው ለማሳካት ሲሉ ያንን ስንኩል ፕሮግራም (ማኒፌስቶ-68) ቀየሱ። ሶስቱም ግምባር ቀደም ጠባብ ብሄረተኞች ያረቀቁት የትግራይ ህዝብ ጥያቄ በመገንጠል እንዲፈታ ያስቀመጠውን ማኒፌስቶ-68 ፅፈው ባስቸኳይ እንዲታተም ወደ ሱዳን ላኩት።

"ሶስቱም ሰዎች ይህንን ከማድረጋቸው በፊት፥ ገና ከተማ እያለን ባዘጋጀነውና የትግራይ ህዝብ ብሄራዊ ጥያቄን በመፍታት ረገድ የድርጅታችን መመሪያ በነበረው ፕሮግራማችን ላይ ለውጥ ለማድረግ የተነሳ ሃሳብ ኣልነበረም። በጥያቄው ዙሪያ በስልትና በስትራተጂ ደረጃ ሙሉ ግንዛቤ ተወስዶ በማያሻማ መንገድ በፅሑፍ ስለሰፈረም መነሳት የነበረበት ጉዳይ ኣልነበረም። ዋናው የመታገያችን መርሆ የሆነውን ሰነድ ፈፅሞ ለመለወጥ ቀርቶ፥ ኣንዳንድ መለስተኛ ማስተካከያ ለማድረግ ቢያስፈልግ እንኳ በጥቂት ሰዎችና በዝግ መድረክ የሚጠናቀቅ ሳይሆን ሰፊ ጥናት ተደርጎበት ለሰፊ ውይይት በሰፊ መድረክ ቀርቦ ድርጅታዊ ውሳኔ ማግኘት ይኖርበታል። ሶስቱም ሰዎች ይህንን የመሰለ መሰረታዊ የፕሮግራም ለውጥ ሲያደርጉ ግን ያመራር ኣካል ሳይመክርበትና ኮንፈረንስ ሳይካሄድበት ወደ ጉባኤም ሳይቀርብ ነው። እነዚህ ሶስት ሰዎችና ሌሎች ስስታም መሰሎቻቸውን ውስጥ ውስጡን በማስተባበር ያቀረቡት ስንኩል ማኒፌስቶ በኣመራሩ ስብሰባ እንኳ ሳይቀርብና ሳይፀድቅ ስዩም መስፍን ለሚባል ሰው ተሰጥቶት ሰነዱን ሱዳን ኣገር ባስቸኳይ ኣሳትሞ ብዛት ያላቸው ቅጂዎች ወደ ሜዳ ላከ።" (የጥቅሱ መጨረሻ።)

ይህንን የመሰለ ጥፋት በፈፀሙ ከይሲዎች ላይ በወቅቱ ለምን ፈጣን እርምጃ እንዳልተወሰደ ኣረጋዊ በርሀ የሚመልሰው ጥያቄ ይሆናል። ይሁን እንጂ፥ ይህንን ከላይ የጠቀስነው ኣስገራሚ ጥቅስ ካንድ ተራ መንገደኛ ሰው እየተነገረን ያለ ምስክርነት ሳይሆን ህወሓትን ከመሰረተና የድርጅቱ ሊቀመንበር ሆኖ ለረጅም ጊዜ ከዘለቀ ሰው መሆኑን በጥሞና ልንገነዘብ ይገባናል።

የትግራይ ሪፐብሊክ የሚባለው ፈሊጥና የህወሓት መሪዎች ይህንን ፈሊጥ ለመተግበር የኤርትራ ነፃ ኣገር ሆና መቀጠል ለምን እንደሚያስፈልጋቸው በማጣቀስ ሌሎች ብዙ ጭብጦች ሊያስገኙ የሚችሉ የሰነድ ማስረጃዎች ማቅረብ እንችላለን። ይሁን እንጂ፥ እስካሁን ድረስ ያቀረብናቸው የማከራከሩ መረጃዎች የኤርትራ መንግስት የባድመ ግጭት ከመከሰቱ በፊት የፌደረሽን ሃሳብ ለማቅረቡና፥ ይህንኑ የፌደረሽን ሃሳብ መለስ ዜናዊ እንዳልወደደውና ያልወደደበት ምክንያትም በማብራራት በቂ ናቸው ብለን እናምናለን። ለማጠቃለል ያህል ግን፥ ትንሽ ገፋ ኣርገን ለማመላከት የምንፈልገው፥ በህወሓትና በወያነ ውስጥ ወሳኝ ስልጣን በመቆጣጠር የተደሰገሰጉት የኤርትራ ዝሪያ ያላቸው ሰዎች (ኣብረዋቸው ያሉ ጥቂት የዋህና ያልነቁ የትግራይ ተወላጆች ባይታጡም) ድብቅ ዓላማ ሁለት ኣጀንዳ ያለው መሆኑን ነው።

---

[12] ይህ ቡድንና ተባባሪዎቹ፥ ሁሉንም የኤርትራ ዝሪያ የሌላቸው ንፁህ የትግራይ ተወላጆችየሆኑ ያመራር ኣባላትን ከጥቅም ውጭ ኣድርጎ በማሸቀንጠር፥ ባሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ምድር ስልጣኑን በብቸኝነት ተቆጣጥሮ ይገኛል። (መለስ ብዙዎች መለሶችን ኣሰልጥኖና ተክቶ በሞት ከመለየቱ በቀር።) እጅግ የሚገርም ኣይደል?

1. የመጀመሪያው አጀንዳ አስቀድሞ የኤርትራን ነፃነት ማረጋገጥ ነው። ይህንኑ አጀንዳ ምንም ዓይነት የህዝብ ውክልና ሳይኖራቸው፥ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል[13] የሚባለውና አሁን በኢትዮጵያ ምድር ህገመንግስታዊ መብት ሆኖ የሚገኘው መብት ገና ሳይደነገግ፥ በተጭበረበረ መንገድ ቢሆንም የራሳቸው ፓርላማና ቋሚ መንግስት ሳይቆም ተሯርጠው ተግባራዊ አድርገውታል።
2. ሁለተኛው አጀንዳቸው ደግሞ እስከቻሉ ድረስ የኢትዮጵያን ሃብት እየመጠመጡና መፃኢቷ ነፃ ትግራይ የምትቋቋምበትን በቢልዮኖች የሚቆጠር ገንዘባቸውን በውጭ አገር ባንኮች እያከማቹ በኢትዮጵያ ስልጣን ተቆጣጥረው ይቀጥላሉ። ይህንን ስልጣናቸውን የሚያስጥል አደጋ ከገጠማቸው ግን፥ የኢትዮጵያ መፈጠሪያ የሆነችውን ትግራይ ገንጥለው ከአማራ በስተቀር የኔ ነው ብሎ የሚማጎትለት ብዙ ሰው የሌለው "ኢትዮጵያ" የሚለውን ስም ለምትገነጠዋ ትግራይ አልብሰው ትግራይን "አዲሲቷ ኢትዮጵያ" ብለው ሰይመው እንደሚሸመጥጡ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው።

እንግዲህ ከኤርትራ መንግስትና ህዝብ ጋር የሚደረግ ግኑኝነትና ትብብር አስፈለጊና ወቅታዊ ሆኖ ያገኘነው፥ ባለፈው ምዕራፍ-አንድ[14] እና በዚህ ሁለተኛው ምዕራፍ ባቀረብናቸው መረጃዎች ተሞርክዘን የህወሓት መሪዎች እርኩስ ዓላማ ማክሸፍ የሚቻልበት መንገድ እሱ ብቻ መሆኑን አውጥተን አውርደን በመገምገም ነበር። የሚያዳምጠን ሰው ግን በወቅቱ አልተገኘም። ያሳዝናል። ለምን እንደሚያሳዝን ትንሽ አንበል።

ትግሉ የሚጠይቀው ነገር ካለ ይህንን በታኝ አጀንዳ ተፈፃሚነት እንዳይኖረው የትግራይ ህዝብ መወረፍና "ካንሰር ነው" ብሎ ማዋረድ ታግቶ የህወሓት መሪዎችን አጀንዳ በማክሸፍ ከፍተኛ ሚና ያለውን የትግራይ ህዝብ ማቀፍ ያስፈልጋል ብለን የአማራ ሊሂቃንን ለማሳመን ፈፅሞ ያልተቻለን ከባዱ የቤት ስራችን ነው።

የአማራ ኤሊቶች በሽታ ኢትዮጵያ ከኛ በላይ የሚቆረቆርላትና የሚያስብላት ሌላ ሰው የለም ብለው ስለሚያስቡ (እንዲያውም "ኢትዮጵያን የሰራት አማራ ነው" የሚሉንም አልጠፉም)፥ ከአማራ ውጭ ሌላ ሰው ተቆርቋሪ ኢትዮጵያዊ ሆኖ ቢያስረዳቸውም እንኳ ሃሳቡን አዳምጠው መመርመርና ማስላት የማይፈቅዱ መሆናቸው ነው። እኛ ደግሞ ከፋም በጀ የትግራይ ህዝብ ስትራተጂካዊ ወገን የአማራ ህዝብ ነው ብለን ስለምናምንና ትክክልም ስለሆነ፥ የነዚህ ወገኖቻችን አጉል መተራመስና ትጥቅ/ዝግጅት የለሽ ባዶ ፉከራና ሽለላ ለደጉና መከረኛው የአማራ ህዝባችንም ሆነ ለምንቆረቆርላት አገር የማይበጅ በመሆኑ የአማራ ሊሂቃን ወገኖቻችንን አበክረን ስንወቅሳቸው ኖረናል። ለወደፊቱም ሽውራራ አመለካከታቸውና ባዶ ፉከራቸው እስከሚገታና ሰከን ብለው የተቆርቋሪ ወገኖቻቸው ተግሳፅና ምክር ምን ይዞት እንዳለው ተረድተው አደብ እስኪገዙ ድረስ ወቀሳችን ከመሰንዘርና አቤቱታችንን ጥፋት በላዩ ላይ ላንገበበው የአማራ ብሄር ህዝባችን ከማቅረብ አንቦዝንም። ይቺን አጋጣሚ በመጠቀም፥ የአማራ ሊሂቃን ወገኖቻችንን ለመውቀስና በተሳሳተ መንገድ ሲነጉዱ ከዚያ የተሳሳተ መንገድ እንዲታቀቡ የምንወተውትበት ምክንያት ባጭሩ ጠቅሰን እናልፋለን።

አንድ ሰው ሚስቱ፥ አህቱ/ወንድሙ፥ ልጁ፥ ባጠቃላይ የስጋ ዘመዱና የቅርብ ወዳጁ የሆነ ሰው ሲያጠፋ ወይም መንገዱን ሲስት ተደብቆ አያማውም ወይም በስህተቱ አይሳለቅም። ወገኑ የሆነው ሰው ሲሳሳት መጀመሪያ ይመክረዋል፤ ስህተተኛ መሆኑንም ያስረዳዋል። ያ

---

[13] የህወሓትና የወያነ መሪዎች የኤርትራ ነፃነት የተረጋገጠው "የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት" መርሆ ነው ይሉናል። ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትለይ ግን ያ መብት በኢትዮጵያ ምድር በህግ የተደነገገ መብት አልነበረም። መብት ሆኖ ከተደነገገ በኋላ ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ ዕድሉ የሚወሰንለት በጥቂት የወያነ መሪዎችና ካድሬዎች አማካኝነት ነው።

[14] http://www.awrambatimes.com/wp-content/uploads/Dialogue_with_Ginbot-7_P2_sec_1.pdf

ወገኑ ልጅ ወይም ታናሹ ከሆነና ምክሩንና ተግሳፁን አላዳምጥ ካለው  ምናልባትም (ዛሬ "በሰለጠንበት/በሰየጠንበት" ወቅት እየቀረ ቢሆንም) እጁ ሊሰነዘርበትም ይገደድ ይሆናል። በዕድሜ የሚበልጠው ወይም ተመጣጣኝ ዕድሜ ያለው አዋቂ ከሆነ ደግሞ እጁን ለመሰንዘር ባይቃጣም ጆሮው እስኪሰነጠቅ ድረስ ሊጮህበት ይገደዳል። ታላላቆቻችንና ወላጆቻችን አልፎ አልፎ በኃይለቃል የሚያስተናግዱን ወይም የሚቀጡን ስለሚጠሉን ወይም ሊጎዱን ስለሚፈልጉን ሳይሆን ስለሚወዱንና ከስህተት ከጥፋት እንድንታቀብ ስለሚያስቡልን ብቻ ነው። ይህ በቅዱሳት መፃሕፍቶቻችን ጭምር የሰፈረ የህይወት መመሪያ ነው።[15]

በአንፃሩ ደግሞ የማያውቀው ወይም የማይዛመደው ሰው ተመሳሳይ ጥፋት/ስህተት ሲፈፅም የሚመለከት ሰው ግን ያንን የማያውቀውን ሰው ምናልባት ለመገሰፅ ይሞክር እንደሆነ እንጂ ከዚያ ኣልፎ ግን ከተሳሳተው/ካጠፋው ሰው ጋር የሚዳረቅበት ምንም ምክንያት ሊኖረው ኣይችልም።

ስለሆነም፥ ከኣማራ ሊሂቃን ወገኖቻችን ጋር የምንዳረቀው፥ በኢትዮጵያ ምድር የበቀሉት ሁሉም ህዝቦች ወገኖቻችን ቢሆኑም፥ በተለየ ታሪካዊና ተፈጥሮኣዊ ምክንያት የትግራይና የኣማራ ህዝብ ኢትዮጵያን በወረፋ እየተቀባበለ ለመግዛት ሲል በስልጣን ከሚሻኮት በቀር መጥፊያውም መዳኛውም መንገድ ኣንድ ስለሆነ፥ የትግራይ ኤሊቶች ሲያጠፉ እንደምንቃወማቸውና እንደምንዋጋቸው ሁሉ ኣማራ ነን የሚሉ ፍጥረቶች ሲያጠፉም እነሱንና ኣገራችንን ከጥፋት ለማስጣል ካለን ቁጭት ተነስተን ያለ ምንም ምህረት እንወቅሳቸዋለን፤ እንገስፃቸዋለን። ከዚህ ውጭ፥ በማጠያይቅ ሆኔታ፥ ኢትዮጵያዊያን ነን ብለን በፅናት የምናምን እኛ የትግራይ ተወላጅ ዜጎች እንደ ህወሓት መሪዎች በኣማራ ጥላቻ[16] በሽታ የተለከፍን ሆነን ሳይሆን፥ ከኣማራ ኤሊቶች ጋር ያለን ግብግብ "ላም እሳት ወለደች፤ እንዳትልሰው ነደደች፥ እንዳትተወው ደግሞ ወለደች" ከሚል ኣገራዊ ብሂል የሚመነጭ ለመሆኑ በሚገባ መታወቅ ያለበት መሆኑን ከታላቅ ትህትና ጋር ባጭሩ ጠቁመን እናልፋለን።

ሁለተኛውና ኣደገኛው የህወሓት መሪዎች ኣጀንዳ (ትግራይን የመገንጠል ኣጀንዳ) ስንመረምር በኢትዮጵያ ምድር የሚኖሩትን ህዝቦች ከዚህ ኣጀንዳ ጋር በትይዩ ኣስቀምጠን መሆን ይኖርበታል። ለምሳሌ ያህል፥ ብዙ ታሪካዊ ችግሮች ያለባቸውን ኣንዳንድ የኢትዮጵያ ክልሎች ግምት ወስጥ ኣስገብተን ብንመረምር የህወሓት መሪዎች ሁለተኛ ኣጀንዳ በኦሮሚያና በኦጋዴን ገበያ በቀላሉ ሸማች ማግኘት የሚችሉ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል። (ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በተኣምረኛው ምርጫ-97 ማግስት የተከሰተውን በማጣቀስ በቀጣዮቹ መጣጥፎቻችን በ"ከፍል 7 እና 8 ላይ ኣስገራሚ የሆነ ታሪክ ኣከለን እንመለስበታለን።) ይህ ግብይት ግን በኦሮሚያና በኦጋዴን ክልሎች ብቻ የሚወሰን ሳይሆን፥ በሌሎች ክልሎች ህዝቦች ገበያዎችም ቢሆን ኣማራጭ ከማጣት የተነሳ ተቀባይነት ያለው ኣጀንዳ ነው። የህወሓት መሪዎች ትግራይን "ኢትዮጵያ" የሚል ስም ኣከናንበው ሲገነጠሉና፥ ልክ ለኤርትራ እንዳደረጉት ለኦሮሚያና ለኦጋዴን እውቅና ሲሰጡ የኣፋር፥ የሲዳማ፥ የቤንሻንጉል፥ የጋምቤላ፥ ወዘተ. ህዝቦች ኣጀንዳውን ይቃወማሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው። በዚህ ሂሳብ ይህንን ኣጀንዳ የማይዋጥለት የኣማራ ህዝብ ብቻ ይሆናል ማለት ነው። እዚህ ላይ ኣንኳሩ ጥያቄ የትግራይ ህዝብስ ምን ይላል? የሚል ጥያቄ እንደሚሆን ኣያጠያይቅም። እናም፥ ይህንን ጥያቄ በሌሎች መጣጥፋችን ተገቢ ስፍራ ተሰጥቶት በዝርዝር የሚቀርብ ቢሆንም፥ የህዝባችንን ኣእምሮ ለማዘጋጀት ያህል ለጊዜው ባጭሩም ቢሆን እንዳስሰዋለን።

---

[15] መፅሓፈ ምሳሌ፤ 23፥13፤ ዕብራዊያን፤ 12፥11።

[16] በጫካው ዘመን በህወሓት መሪዎች ተደርሶ ሲዘመርና ኣቁሙ ሲባሉ "የሸዋ ትግሬ" ያስብሉ ከነበሩት በርካታ ግጥሞች ኣንዱ እንዲህ ይላል። "ተልዓል ተበገስ ተጋዳላይ ትግራይ፤ ኣርኪብካ በሎ ነቲ ዓሻ ኣምሓራይ።" ትርጉም፤ "ተነስ ተንቀሳቀስ የትግራይ ታጋይ፤ ኣሳደህ ምታው ያንን ቂል ኣማራ።" (ትችት፤ ኣሳደን መምታቱን ባንወደውና የምንቃወመምው ቢሆንም ያማራ ሊሂቃን ቂልነት ግን በተግባር የተመሰከረ ሆኖ ኣግኝተነዋል።)

ሁለተኛውን የህወሓት መሪዎች አጀንዳ በተመለከተ ከአማራ ኤሊቶች ጋር በመሰረቱ ብዙ ልዩነት የለም። የአማራ ኤሊቶችና (ጥቂት የህወሓት መሪዎች አደንዛዥ መርፌ ያልተወጉ የትግራይ ኤሊቶች ጭምር) ችግር "የህወሓት መሪዎች አጀንዳ ትግራይ ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ያቀደ መሆኑን ቢረዱ ወይም ቢገምቱም ቅሉ፥ "የትግራይ ህዝብ ይህንን እንዲያደርጉ ለህወሓት መሪዎች አይፈቅድላቸውም ወይም ይዋጋቸዋል" በሚል ቅዠት ይዋዥቃሉ። ይህ አመለካከት የሚመነጨው የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያዊነት ጥያቄ ላይ ያለውን የማያወላዳ አቋም ከመገንዘብ የሚመነጭ መሆኑን መረዳት ቢቻልም፥ የግንዛቤው መንደርደሪያ በራሱ ግን እያንዣበበ ያለውን አደጋ በመቋቋም ረገድ ምንም አስተዋፅኦ/አቅም የለውም። ይህ የሚያመለክተው የትግራይ ህዝብ ይህንን ለመከላከል ምንም ዓይነት አቅም የሌለውና፥ ከግራም ከቀኝም የተወጠረ ህዝብ ከመሆኑ የተነሳ ህልውናው በህወሓት ህልውና ላይ የተመሰረት እንዲሆን የተደረገ ህዝብ መሆኑን፥ የሁሉም ነገሮች አስተርጓሚ በሆኑት በአማራ ኤሊቶች ዘንድ በቂ ግንዛቤ የሌለ መሆኑን ነው። ስለሆነም፥ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ (በ"ክፍል II ላይ በሰፋት የምንመለስበት ቢሆንም)፥ የትግራይ ህዝብ የሚገኝበትን ሆኔታ ለማመላከት ያህል አንዳንድ ነጥቦች ጠቅሰን በጥቂት ቃላቶች ለመግለፅ እንሞክራለን።

1. የኤርትራን ጉዳይ አስመልክቶ የህወሓት መሪዎች የፈፀሙት ሁሉ (የድንበር ግጭቱ ያስከተለውን ጦርነት አያያዝ ጨምሮ) በኢትዮጵያ ምድር ካሉ ማናቸውም የህብረተሰብ ክፍሎች በበለጠ የሚቃወመውና የሚያበሳጨው የትግራይ ህዝብ መሆኑን ትግራይን በመንብኘት ማረጋገጥ ይቻላል። ነገር ግን እስካሁን ድረስ የወያኔ መሪዎችን ከቦታቸው አንዲት ስንዝር ታክል እንኳ ንቅንቅ ሊያረጋቸው አልቻለም። ስለዚህ፥ የወያኔ መሪዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኙት በህገ መንግስቱ በተሰጣቸው ሙብት መሰረትና፥ እነሱ መቶ በመቶ በሚቆጣጠሩት የትግራይ ክልል ፓርላማ አማካኝነት ትግራይን እንገንጥል ሲሉ የትግራይ ህዝብ ያቆማቸዋል ብሎ ማሰብ እጅግ አዘናጊና ገዳይ አመለካከት ነው።
2. የቀድሞ የህወሓት ከፍተኛ መሪዎች (እነ ተወልደ፥ ገብሩ አስራት፥ ስየ አብርሃ፥ ወዘተ.) የኤርትራ ጉዳይ አያያዝን ጨምሮ ሌሎች ይዘዋቸው የተነሱት ጥያቄዎች የራሳቸው ጥያቄዎች ብቻ ሳይሆኑ የመላው የትግራይ ህዝብ ጥያቄዎች ነበሩ። ታዲያ ጥያቄው የመላው ህዝብ ጥያቄ ሆኖ ሳለ ለምን የትግራይ ህዝብ ሰዎቹን ከነመለስ ዱላ ሊያጥላቸው አልቻለም? ከዚህ በተጨማሪ፥ ሰዎቹ (እነ ስየ፥ገብሩ፥ተወልደ፥ ወዘተ.) በህዝብ ተመርጠው የፓርላማ አባላት ስለነበሩና ከህወሓት ሲባረሩ ከፓርላማም ስለተባረሩ፥ ለምን የመረጣቸው ህዝብ ተወካዮቻችንን ከፓርላማ ማባረር አትችሉም ብሎ አልተዋጋላቸውም?
3. ባለፉት ሃያ ዓመታት ሌሎች ኢትዮጵያዊያን (ባብዛኛው የአማራ ሊሂቃን) በትግራይ ህዝብ ላይ ከረጩት መጠነ ሰፊ የጥላቻ ፕሮፓጋንዳ አንፃር የትግራይ ህዝብ ከህወሓት ውድቀት በኋላ የሚኖረው ዋስትና በምንና በማን ይረጋገጣል? ሌትና ቀን ሳይሉ የሚታገሉና በራሳቸውና አገርቤት በሚኖሩ ዘመዶቻቸው ላይ ብዙ መከራ እየተቀበሉ ያሉ እውቅ የትግራይ ህዝብ ታጋይ ልጆች ላይ (እነ ስየ አብርሃና እነ ገብሩ አስራት፤ ዛሬ ደግሞ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ምንም ወንጀል ያልፈፀሙትና የወያነ መንግስት ሰለባ ከመሆን አምልጠው በስደት የተቀላቀሉን ወንድሞቻችን እነ ወጣት ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ ሳይቀሩ)፥ በዘረኛ አማሮች የሚወረወርባቸው ጦርና የሚመዘዝባቸው ሰይፍ እያየ፥ እየሰማ፥ እያነበበና፥ እየታዘበ ያለው የትግራይ ህዝብ ህወሓትን ጠልቶ የልጆቹን አሳዳጆች የሚመርጥበት ምን ምክንያት አለው?

እንዲህ እያልን ብዙ ነጥቦች መጥቀስ እንችላለን። ሆኖም በሌሎች መጣጥፎቻችን በበለጠ ስለምናብራራው ለዛሬ ይህንን የሚበቃን ይመስለናል። ይህንን መጣጥፍ ለማጠቃለል ግን፥ ለዚህ መጣጥፍ መነሻ ምክንያት ለሆኑንና ዋና አጃቢዎቻቸው ያማራ ኤሊቶች ለሆኑለት ለግንቦት ሰባቶች መሪዎች እንደተለመደው መልእክታችን እነሆ!

ባለፉት መጣጥፎቻችን ያቀረብናቸው ቁምነገሮችና በዚህ መጣጥፍ አማካኝነት እያቀረብናቸው ያሉት ጠቃሚና ወሳኝ ጭብጦች በበኩላችን አምቀንና ከህዝብ ደብቀን አላስቀመጥናቸውም። በመሰረቱ፥ ማንኛውም አገርንና ህዝብን የሚመለከት ጉዳይ ከህዝብ ጀርባ ተደብቆ ማከናወን አይቻልም፤ አይገባም። ስለሆነም ይህንን አሁን እያቀረብነው ያለ ጭብጥ በተገቢው ጊዜ (ከአስራ ሁለት ዓመታት በፊት) "የኤርትራ

ፋይል ሲከፈት" በሰሰኘ ሰፊ መድብል በተከታታይ እትሞች ታዋቂና ተነባቢ በሆኑ ያገሪቱ የግል ሚዲያዎች ኣማካኝነት በግልፅ ለህዝብ ይፋ ኣድርገናል። ከዚህ በተጨማሪ ኣገሪቷ ኣሏት ከሚባሉ ያገር ሽማግሌዎችና የተቃዋሚ ኃይላት ጋር መክረንበታል። ኣስመክረንበታል። የሽማግሌዎች ምክር ቤር ተቋቋሞ፥ በሌለ ኣገርና ስልጣን እርስ በርስ የሚቦጫቸቁትን የተቃዋሚ ኃይላት ተብየዎች በጋራ ሆነው ይህንን ጉዳይ ከዳር እንዲያደርሱ ጊዜያችን፥ ጉልበታችንና ያለችን ደካማ ገንዘባችን ኣፍስሰንበታል። ይህ ሁሉ ኣድርገን ውጤት ያልተገኘበት ምክንያት ግን ዛሬ ላይ ነገሮች እንደ ጥዋት ውሃ ኮለል ብለው በጠሩበት መድረክ ላይ ሆነን ኣፋችንን ሞልተን ስሞታችንን ለምንታገልለት ህዝብ ይፋ እንድናደርግ እንገደዳለን። ምንም እንኳ እየቀጠሉ ባሉ መጣጥፎቻችን በ"ክፍል ኣራት" ላይ ከኤርትራ በኩል የተገኘውን ጭብጥ ለማስፈፀም ሲባል በመጠናቀቅ የነበረውን "የሽማግሌዎች ምክር ቤት" የተስተጓጎለበትን ሆኔታ ስንገልፅ በሰፋት የምንመለስበት ቢሆንም፥ እዚህ ላይ ባጭሩ ስሞታችንን መግለፅ እንፈልጋለን።

ዛሬ በሞተ ሰዓት ላይ ግንቦት ሰባቶች በኤርትራ በኩል ተኣምር ይሰሩልናል ብለው የሚያሽካኩት ፍጥረቶችና እንደነ ሙሉጌታ ሉሌ ያሉ "ኣንጋፋ ጋዜጠኛ" ተብየዎች ትናንት እኛ በትክክለኛው ጊዜና መንገድ ልንሰራው ያቀድነውን ኣንገባቢ ስራ ሲያደናቅፉና ሲያበላሹ የነበሩቱ መሆናቸውን ስንመለከት ባንበሳጭም በመገረም እንደመማለን። እየተገረምናና እየተደመምን ደግሞ ደግነቱ የማያልቅበት ፈጣሪያችን ዕድሜ ሰጥቶን የትናንቱ ኣውጋዦቻችንና ኣደናቃፊዎቻችን ጭቃ ውስጥ ተዘፍቀው የኢሳያስ ኣፈወርቂ ኣሞጋሾችና ተነጣፊዎች ሆነው መገኘታታቸው ስናይ በእጅጉ እንደሰታለን። እንኮራለንም!

ከደስታችንና ከኩራታችን ጎን ለጎን ግን ኣገራችን እንደነዚህ ያሉ ማፈሪያ የሆኑ ሰዎች ማብቀሏ ደግሞ ያሳዝነናል። ከነዚህ ኣሁን ግንቦት ሰባትንና ኢሳያስ ኣፈወርቂን እየካቡና እያወደሱ ካሉት ጉዶች ኣብዛኛዎቹና ዋናዎቹ በፀሃዩ ንጉሳችን ዘመንና፥ የነሱ ሰላባ የሆነው የደርግ ስርዓት በነበረበት ወቅን ኣንዲት ቃል ሳይተነፍሱ ኣድፍጠው የስርዓቶቹ መሳሪያና ጋሻጃግሬ ሆነው ጮማቸውን እያማረጡ ሲቆርጡና ዊስኪያቸውን ሲጨልጡ የነበሩ መሆናቸውን ስለምናውቅ ደግሞ ይገርሙናል። የትናንቱ ጮማ ኣስቆራጭ ሄዶ ዛሬ ሌላ ጮማ ኣስቆራጭ ብቅ ሲል ለቀም ማድረጋቸው የሚጠበቅ ነው። እነዚህ ኣገር ኣሰዳቢዎችና የህዝብ ጠሮች ዛሬ ላገርና ለህዝብ ተቆርቋሪዎችና ታጋዮች መስለው የሚወራጩት እውነት ታጋዮችና ተቆርቋሪዎች ሆነው ሳይሆን፥ ያንን የለመዱት ድሎትና ምቾት ስለጎደለባቸውና "ትግሬ ነገሰ" ከሚል ቁጭታቸው በመነሳት እንደሆነ ካሁን በፊት የፃፏቸውና የፈፀሟቸው ድርጊቶች ኣስረግጦ ማስረዳት ለኛ እጅግ ቀላል የቤት ስራ ነው።

የ"ትግሮች ነገሱብን" ኣባዜያቸው የሚጋለጠው ደግሞ ኣገር የሚያጠፋውን የወያነ ኣመራር በመቃወም ሳይሆን፥ "ከኑግ ጋር የተገኘህ ሰሊጥ ኣብረህ ተወቀጥ" እንዲሉ፥ ኣብርሃም ያየህን ጨምሮ ሁሉም የትግራይ ተወላጅ የሆነውን ሁሉ በማቀላቀል ጠላት ነው በሚል ፈሊጥ የተጨማለቀ ነው። ይህ ፈሊጥ ደግሞ ኢትዮጵያን ከሚበትን በቀር ሌላ ፋይዳ የለውም። ለነገሩ ኢትዮጵያ ብትበተን ምን ገዷቸው! ጉዳቱ ለኛ ይተርፈን እንደሆነ እንጂ እነሱማ የፈረንጅ ኣገርና ዜግነት ኣዘጋጅተው የለ! እኛ በእግዚኣብሔር ድጋፍ ብዙ ደክመንና ጥረን ያስገኘነው ጠቃሚ ግኝት የተስተጓጎለውም ከዚህ የመከነና ኣፍራሽ ፈሊጥ የመነጨ ነው። እኛ የሰራነው ታላቅ ስራ ያመከኑት ያማራ ኤሊቶችም "ኤርትራን ያስወሰዱ ኣፄ ምኒልክ ናቸው ብለው የሚከሱን ትግሮች ኤርትራን ከሚያመጡልን ትቅርብን፤ ወይም ደግሞ ትግሮቹ ያስወሰዷትን ኤርትራ የምትመለስ ከሆነም በኛ ባማራዎቹ ብቻ መሆን ኣለበት" ያሉትም ያንን ኣፍራሽ የእብዶች ፈሊጣቸው የወለደው ኣባዜ ነበር።

ይህ የእብዶች ፈሊጥ ለማስቀጠል ዛሬ ባለቀ ሰዓትና ከኣስራ ሁለት ዓመታት በኋላ ብዙ ነገሮች በተለዋወጡበት ወቅት ኣዲስ ተኣምር ሰሪዎች የተገኙ ይመስል ባለ ፈሊጦቹ ለማንገራገርና ለመጨፈር ፈቃድ መጠየቅ ባያስፈልጋቸውም የትም እንደማይደርሱ ግን ከኣሁኑ ልናረጋግጥላቸው እንወዳለን።

ይህንን መጣጣፍ የምንቋጨው ኣጭር መልእክት በማስተላለፍ ነው። ግንቦት ሰባቶች በጉራና በፉከራ ከየዋህ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ብር መዛቅ ይችላሉ። ይህ ቀላል ነው። በዚያ ብር ልክ ግን ፈተና ይጠብቃቸዋል። ይህንን የሚያፍሱት ብር በተላለፉት የግንቦት ሰባቶች ዲስኩሮች መሰረት በመሬቱ ላይ ባጭር ጊዜ ተጨባጭ ቁምነገር ካላስገኘ ብሩ እሳት ሆኖ እንደሚለበልባቸው ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው። እኛ ይህ እንዲሆን ባንፈልግም ውጤቱ ግን ይህ እንደሚሆን ኣንጠራጠርም። ስለዚህ፥ ይህ ከመሆኑ በፊትና ኋላ ደብቁኝ ሰዉሩኝ ማለት ሳይመጣ፥ ከኤርትራ መንግስትና ህዝብ የሚደረግ ማንኛውም ግኑኝነትም ሆነ ትብብር ፋይዳ የሚኖረው ከሆነ፥ ግንቦት ሰባት ትህዴን በተባለ የትግራይ ፈረስ ተፈናጦ በመጋለብና የሻዕቢያ ጎራዴ ኣንግቶ ኣካኪ ዘራፍ በማለት ሳይሆን፥ ካገር ሸማግሌዎችና ወሳኝ ሚና ካላቸው የፖለቲካ ኃይሎች ጋር በመመካከር፥ በተለይ ደግሞ የቀድሞ የህወሓት መሪዎች የነበሩትን በማማከርና በማሳተፍ ብቻ መሆን እንደሚገባው ኣስታውሰን ኣንባቢዎቻችን በትህትና እንሰናበታለን።

<u>በመጨረሻ ከልብ የመነጨ ምስጋና</u>

ከቅርብ ቀናት በፊት ያስተላለፍነው ማስታወቂያ መሰረት በማድረግ ባለፉት ሁለት ሳምንታት በተከታታይ የለቀቅናቸውን ሁለት ኣበይት ጉዳዮች ያዘሉ ፅሑፎቻችንን በጥሞና ኣጢናችሁ ምስጋና ለለገሳችሁንና ላበረታታችሁን እጅግ በርካታ ወገኖቻችን ከልብ የመነጨ ምስጋናችን ይድረሳችሁ። ለወደፊቱም ምክራችሁና ድጋፋችሁ፥ ጉድለት ሲኖርም ተግሳፃችሁ፥ እንዳይለየን በታላቅ ትህትና እንጠይቃለን። ከሁሉም በላይ ያስደሰተንና ያስፈነደቀን ግን የኣማርኛ ቋንቋ ኣቅማችን መዝናችሁ ከፍተኛውን የማለፊያ ቁጥር/ማርክ ሰጥታችሁ ያበሰራችሁን ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን ያደረጋችሁት መልካም ተሳትፎ ነው። ሰለ ኣማርኛ ቋንቋ ትንሽ እንናገር፡

ቋንቋ የሁሉም ነገር መክፈቻ ቢሆንም በተለየ የሃሳብ ማሸጋገሪያ ድልድይ ነው ቢባል ስህተት ኣይሆንም። እኛ የትግራይ ሰዎች የኣማርኛ ቋንቋ የራሳችን ቋንቋ ነው ብለን ወደንና ፈቅደን የተቀበልን ህዝብ ነን። ይህ ፈቃደኛነትን ብቻ የሚወክል ነው። ብቃትን ግን ኣያጎናፅፍም። ምንም እንኳ የትግራይ ልጆች በትምህርት፥ በንባብ፥ በስራ መስክና በመሳሰሉት መስመሮች ከልጅነት ጊዜ ጀምሮ ላማርኛ ቋንቋ እንግዳ ባይሆኑም፥ ቋንቋው የኣፍ መክፈቻ ቋንቋቸው ባለመሆኑ፥ ቋንቋውን በሚገባ ቢረዱትም ሲፅፉት ግን ብዙ ችግር ያጋጥማቸዋል። እኛም የዚህ ችግር ሰለባ ሆነን እንደሆነ ራሳችንን ስንጠይቅ ቆይተናል። ምክንያቱም፥ ለረጂም  ጊዜያቶች ጉልበታችንና ጊዜያችንን ሰውተን ባማርኛ ቋንቋ ያሸጋገርናቸው ምክሮችና ተማፅኖዎች ሰሚ ጆሮ ማጣታቸውን ስንመለከት ምናልባት የቋንቋ ቅንብራችን ለቋንቋው ባለቤቶች የማይገባ ሆኖ ይሆናል የሚል ስጋት ስለነበረን ነው። ኣሁን ያንን ጥርጣሬያችን ተገቢ ኣቅም ያላቸው ሰዎች ኣስተካክለውልናል። ችግሩም ከቋንቋ የመረዳት ወይም ያለመረዳት የመነጨ ሳይሆን <u>"ከስንፍና፥ ከንቀትና ራስንና ታሪክን ጠንቅቆ ካለማወቅ የሚመነጭ ፍቱን መድኃኒት ያልተገኘለት ችግር ነው"</u> በማለት ስለጠቆማችሁን ስጋታችንን ቀርፋችሁልናል። ለድጋፋችሁ፥ ለኣበረታች መልእክቶቻችሁና፥ ለኣስተምህሮኣችሁ ከልብ እናመሰግናለን።

በመጨረሻም፥ ሁላችሁም እንደመከራችሁን የጀመርነውን ኣድካሚ ስራ በብርታት እንደምንቀጥልና፥ በመጨረሻም ኣሸናፊና ተሸናፊ ሳይሆን ሁሉም ኣሸናፊ የሚሆንበትን የበኩላችን ማእከላዊ ሃሳብ ኣበርክተን፥ ህዝብ የራሱን እርምጃ መርጦ እንዲወስድ ጋብዘን በመሰናበት በቋሚ ስፍራችን ማለትም ከህዝብ ጀርባ ቆመን ህዝብ የወደደውን ምርጫ የምንከተል መሆናችንን ቃል እንገባለን። ለመልካም ምኞታችሁና ምክራችሁ ሁላችሁንም እንደገና እናመሰግናለን።

እግዚኣብሔር/ኣላህ ኣገራችንናንና ህዝባችንን ይጠብቅ! ኣሜን!